# በዝቋላ ገዳም 4 መነኮሳት በታጣቂዎች እንደተገደሉባት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስታወቀች


FB

በዝቋላ ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም

23 የካቲት 2024

**በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ውስጥ በሚገኘው በዝቋላ ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም አራት መነኮሳት የካቲት 14/ 2016 ዓ.ም. በታጣቂዎች እንደተገደሉባት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን**

አስታወቀች።

የተገደሉትም መነኮሳት የገዳሙ መጋቢ አባተክለማርያም አስራት፣ ፀሐፊ አባኪዳነ ማርያም ጥላሁን፣ የመጽሐፍ መምህርና በቅዳሴ የሚያገለግሉ አባገብረ ማርያም አበበ እንዲሁም በአመክሮ የሚኖሩ መናኝ ኃይለማርያም ወልደሰንበት መሆናቸውንም ቤተ ክርስቲያኗ ትናንት ባወጣችው መግለጫ አስታውቃለች።

ቤተ ክርስቲያኗ ግድያውን የፈጸመው የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ወይም ቤተ ክርስቲያኗ “ኦነግ ሸኔ” ብላ በጠቀሰችው ታጣቂ ቡድን እንደሆነም ገልጻለች።

ሶስቱ መነኮሳቱ የካቲት 11/2016 ዓ.ም. በ“ኦነግ ሸኔ” ታጣቂ ቡድን ታግተው ወደ በረሃ ከተወሰዱ በኋላ የታገቱትን ለማስለቀቅ ገዳሙ ጥረት በሚያደርግበት ወቅትም ተጨማሪ መነኮሳትን አግተው መውሰዳቸውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቴሌቪዥን በድረ ገጹ አስታውቋል።

ከታገቱትም መነኮሳት ውስጥ በትናንትናው ዕለት አራቱ የተገደሉ ሲሆን፣ አባ ኪዳነማርያም ገብረ ሰንበት የተባሉት መነኩሴ ቆስለው በገዳሙ እንደሚገኙም ቤተ ክርስቲያኗ በመግለጫዋ አስፍራለች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በአርሲ 36 ምዕመኖቿ መገደላቸውን አጥብ...
5 ታህሳስ 2023

በምዕራብ ኦሮሚያ ዘጠኝ ምዕመናን ከቤተ ክርስቲያን በታጣቂዎች ተወስደው መገደላቸው...
1 ታህሳስ 2023

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ በቤተክርስቲያኗ ላይ ጥቃት እየተፈጸመ ነ...
5 የካቲት 2023

በአሁኑ ወቅትም ታጣቂዎቹ ወደ ገዳሙ ለመግባት እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት መንገድ እንዳይፈጠር እንዲሁም መነኮሳቱ እና የገዳሙ ቅርስም አደጋ ላይ እንዳይወድቁ የፌደራል እና የክልሉ የፀጥታ አካላት እንዲታደጓትም ጥሪ እና አደራ አቅርባለች።

በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ የሚገኘው የዝቋላ ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ከጥንታዊያን እና ታሪካዊ ገዳማት መካከል አንዱ ነው።

በዚህ ገዳም በርካታ መነኮሳት እንዲሁም ቅርሶች የሚገኙበት ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት ዘረፋ፣ ቃጠሎ እና ከባድ ጉዳቶችን እንደደረሰበትም የቤተ ክርስቲያኗ መግለጫ አስታውሷል።

ቤተ ክርስቲያኗ መነኮሳቷን ገድሏል ያለችው መንግሥት ሸኔ እያለ የሚጠራው የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት በግድያው ዙሪያ እካሁን ያለው ነገር የለም።

## ተያያዥ ርዕሶች

ሃይማኖት

ኢትዮጵያ

ክርስትና

## እንዳያመልጥዎ

**አሜሪካዊው ሮበርት ፕሪቮስት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተመረጡ**

ከ 9 ሰአት በፊት

**"ሐኪም በመሆኔ ያተረፍኩት ድኅነትን ነው" የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎች እሮሮ እና ጥያቄ**

8 ግንቦት 2025

**በቀጠለው ግጭት ውስጥ ፓኪስታን 25 የሕንድ ድሮኖችን መትታ መጣሏን ገለፀች**

8 ግንቦት 2025

## ከየፈርጁ



እንደ ካንሰር፣ ስኳር እና የልብ ድካም ያሉ ህመሞችን ለማወቅ የሚረዳው የጆሮ ኩክ

6 ግንቦት 2025




ቢቢሲ አማርኛ ዜና